2

# በትራንስፖርት ባለሥልጣን
# የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት
# ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት

# የህዝብ ትራንስፖርት
# ማመላለሻ የጉዞ መመሪያ

675/2013

መስከረም/2004 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## 1. መግቢያ

የትራንስፖርት አገልግሎት ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ እንቅስቃሴዎችን በማቀላጠፍ በተለይም የዜጐችን ጥቅምና ፍላጎት መሰረት በማድረግ፣ የባለሐብቱን የልማት ተሳትፎ በማሳደግ፣ የነፃ ገበያ ሥርዓትን በቀጥታ ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በማበረታታት፣ የግብርናውን፣ የኢንዱስትሪውና የአገልግሎት ዘርፉን ትስስር በማጠናከር በአጠቃላይ ድኅንነትን ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋፆ አለው።

በመሆኑም ይህን መመሪያ ማውጣት ያስፈለገው፦

1. የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚዎችን በእኩል ዓይን አለማየት
2. የተሣፋሪዎች መብት ረገጣ የሚታይ በመሆኑ
3. የተገልጋዮችን እርካታ አነስተኛ በመሆኑ
4. የህዝብ ትራንስፖርት ዘርፍ ኦኘሬተሩን የሚያበረታታ ሆኖ ባለመገኘቱ
5. የሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል አቅም ያገናዘበና ተደራሽ አለመሆኑ
6. የተሳፋሪዎችን ዕቃ ማጓጓዝ አስቸጋሪ እየሆነ በመምጣቱ እና
7. የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ከዘመኑ የሀገሪቱ እድገት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ እድገት እያሳየ ባለመሆኑ ነው።

የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚዎችን በእኩል ዓይን በማየትና በማማከል የፆታ፣ የዕድሜ፣ የአካል ጉዳት፣ የዘር፣ የሐይማኖት፣ የጋብቻና የቤተሰብ ሁኔታ ላይ ልዩነት ሳያደርግ የሚሰጥ መሆን አለበት። የተገልጋዮችን እርካታ ለማሳደግ ኦኘሬተሩን፣ አስፈፃሚውን፣ ፈፃሚውንና ተገልጋዮችን ያጠቃለለ የሕግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት በተሻለና ቀጣይነት ባለው መንገድ መስጠት ያስፈልጋል።

የተሣፋሪዎች መብት ሊታለፍ የማይገባው መሰረታዊ ጉዳይ በመሆኑ አገልግሎቱን ለመስጠት ግልፅነት ያለው ሕግ፣ ዘመናዊ ተሽከርካሪ፣ ተገልጋዮችን ያማከለ፣ ኦኘሬተሩን የሚያበረታታ፣ ተሽከርካሪዎች ለኢኮኖሚው ያላቸውን ፋይዳ ግምት ውስጥ ያስገባ፣ ደኅንነታቸው የተረጋገጠ፣ አገልግሎቱ በአካባቢ ላይ ያለውን ተፅኖ የቀነሰ፣ የሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል አቅም ያገናዘበና ተደራሽ እንዲሆን በማድረግ ቀጣይነት ያለው የትራንስፖርት አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል። ለዚህ እውን መሆን ደግሞ

የመሠረተ ልማት አውታር ካልተሟላ አገልግሎቱን ለማሻሻል የሚደረገውን ጥረት በሙሉ ከንቱ ያደርገዋል፡፡

የትራንስፖርት ባለሥልጣን በአዋጅ 468/97 ክፍል ሁለት የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፉን ለማሻሻል ደንቦችንና መመሪያዎችን በማውጣት ማስፈፀም እንዳለበት ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በተለይ በዚህ አምድ ክፍል ሁለት ንዑስ አንቀፅ -ረ "መንገደኞችን፣ ዕቃዎችንና ፖስታዎችን በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት ስለሚጓጓዙበት ሁኔታ መመሪያ ማውጣትና አፈፃፀሙን መከታተል" ለባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ከተሰጡት ተግባራትና ኃላፊነቶች አንደኛው ነው፡፡

በመሆኑም በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ አገልግሎት ዘርፉ የተሣፋሪዎችን መብት፣ ምቾትና ደኅንነት ማረጋገጥ በማስፈለጉ ምክንያት ይህን የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ አገልግሎት የኦፕሬተሮች እና የተሣፋሪዎች መብትና ግዴታ አገር አቀፍ መመሪያ ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

675/2013

## ክፍል አንድ

**ርዕስ፡-**

ይህ መመሪያ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ማህበራት የኦፕሬተሮች እና የተሣፋሪዎች መብትና ግዴታ አገር አቀፍ መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**ትርጓሜ፡-**

***"መናኸሪያ"*** ማለት ለሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች መነሻ፣ መድረሻ እና ማደሪያ ሲሆን፣ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ ቦታ ነው፡፡

***"ረዳት"*** ማለት በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሙያ የብቃት ማረጋገጫ በማግኘት በኦፕሬተሩ ተቀጣሪ ሆኖ በሥራው ላይ የተሠማራ ሰራተኛ ነው፡፡

***"ባለሥልጣን"*** ማለት የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣንና የክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ቢሮዎች ናቸው፡፡

***"የብቃት ማረጋገጫ"*** ማለት በፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም በክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ቢሮዎች በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ አገልግሎት የሚሰጡ ትራንስፖርተሮች ለሚሰጡት የአገልግሎት ደረጃ የተሰጠ መረጃ ነው፡፡

***"ተሣፋሪ/ተጓዥ"*** ማለት በሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ህጋዊውን ትኬት ይዞ የሚጓዝ ግለሰብ ነው፡፡

***"የተሣፋሪ መብት"*** ማለት በህዝብ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ለሚጠቀሙ ተሳፋሪዎች በዚህ መመሪያ መሰረት የተሰጠ መብት ነው፡፡

***"የተሣፋሪ ግዴታ"*** ማለት በሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ የሚጠቀም ሰው በዚህ መመሪያ ውስጥ የተቀመጡትን ግዴታዎች ማክበር ነው፡፡

***"ኦፕሬተር"*** ማለት የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ለመስጠት ተመዝግቦ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው የተሽከርካሪ ባለንብረት ግለሰብ ወይም ድርጅት ነው፡፡

***"የዕቃ ጫኝና አውራጅ"*** ማለት በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መናኸሪያዎች በሕግ አግባብ ተመድበው የተሣፋሪዎችን እቃ ከአውቶብስ የሚያወርዱ ወይም የሚጭኑ ሠራተኞች ናቸው።

***መኪና*** ማለት የህዝብ ትራንስፖርት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ነው።

***ሾፌር*** ማለት የህዝብ ትራንስፖርት ማመላለሻ አሽከርካሪ ነው።

***ዓላማ፡-*** የዚህ መመሪያ ዓላማዎች፡-

1. ተገልጋዮች መብቶቻቸውንና ግዴታቸውን አውቀው ተግባራዊ ማድረግ
2. የሚሰጠው የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አስተማማኝ፣ ፍታዊ፣ ምቾቱና ደኅንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፣
3. የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የተመዘገቡ ማህበራትና ኦኘሬተሮች መብቶቻቸውንና ግዴታቸውን አውቀው ግዴታቸውን ማክበርና መብታቸውን ማስከበር እንዲችሉ ማድረግ
4. የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የተመዘገቡ ማህበራትና ኦኘሬተሮች በሥርዓት እንዲመሩ በማድረግ የተገልጋዩን እርካታ መጠን ማሳደግ ነው።

***የተፈፃሚነት ወሰን፡-*** ይህ የአፃፀም መመሪያ በፌዴራልና በክልል ትራንስፖርት አገልግሎት ለሚሰጡ ባለሐብቶች፣ ማህበራት፣ ኦኘሬተሮችና ተገልጋዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

# ክፍል ሁለት

## የኦኘሬተሮችና የተሣፋሪዎች መብቶችና ግዴታዎች

### 2. የተሣፋሪ መብቶች

1. ማንኛውም ሰው በሕዝብ፣ የንግድ፣ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ህጋዊውን ክፍያ ፈፅሞ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የመንቀሳቀስ መብት አለው፡፡

2. ማንኛውም ተጠቃሚ የፆታ፣ የቀለም፣ የሃይማኖት ወይም የሌላ ልዩነት ሳይደረግበት ሰው በመሆኑ ብቻ በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪ አገልግሎት የማግኘት መብት አለው፡፡

3. ተጓዦች በሚጓዙበት ወቅት በመኪና አደጋ ምክንያት ለሚደርስ የአካል ጉዳት፣ ሞት ወይም ንብረት መጥፋት፣ መበላሸት ወይም ሌላ ጉዳት አስፈላጊውን  ክፍያና የንብረት ካሳ ከኦፕሬተሩ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

4. እስከ ሰባት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሕፃናት በነፃ ከሰባት እስከ አስራ ሁለት ዓመት ያሉት ሕፃናት ደግሞ በግማሽ ክፍያ ከወላጆቻቸው ወይም ከረዳቶቻቸው ወይም ከሞግዚቶቻቸው ጋር የመጓዝ መብት አላቸው፡፡

5. ከአስራ ሁለት ዓመት በላይ የሆኑ ህፃናት ግን ሙሉ ክፍያ ከፍለው ወንበር ላይ ተቀምጠው መጓዝ  ይችላሉ፡፡

6. በአንድ ተሽከርካሪ ውስጥ ግማሽ ክፍያ ከፍለው ከወላጆቻቸው ወይም ከረዳቶቻቸው ወይም ከሞግዚቶቻቸው ጋር የመጓዝ መብት ያላቸው ህፃናት ብዛት ባለሀብቱን በማይጎዳ ሁኔታ ቁጥራቸው መወሰን ስላለበት ተሳፋሪ የማግኘት ዕድሉ 90% ተብሎ ታሳቢ ተደርጎ 60 ተሳፋሪዎች በሚጭን ተሽከርካሪ እስከ  6 ህፃናት ብቻ እንዲጓዙ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ባለሀብቱ እንዳይጎዳ የህፃናቱን ጤንነት ጠብቆ አመቺ በሆነ መልኩ ተጠጋግተው እንዲቀመጡ ማድረግ ይችላል፡፡

7. ከ 2 በላይ ዕድሜያቸው ከ7-12 ዓመት የሆኑ ህፃናት ይዞ የሚጓዝ ወላጅ በዛ ያሉ ህፃናትን በበቂ ሁኔታ መንከባከብ ስለማይችል፣ ለህፃናቱ ምቾት

እና ለመንገድ ደህንነት ሲባል ለሚይዙት ወንበር ሙሉ ክፍያ ከፍሎ በወንበር ላይ ተቀምጠው ሊጓጓዙ ይችላሉ፡፡

8. ልጅ የያዙ ወላጆችና ህፃናት፣ አረጋዊያን፣ ነፍሰጡር ሴቶች፣የአካል ጉዳተኞች፣ለሀገራቸው ታላቅ ስራ የሰሩና ታዋቂ ሰዎች መሆናቸው በህዝቡ የሚታወቁ ሰዎች፣ ለልዩ ስራ የተላኩ የመንግስት ሰራተኞች እና የታመሙ ሰዎች ቅድሚያ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

9. ተሳፋሪዎች ከመነሻ እስከ የወቅቱን ታሪፍ ያለተጨማሪ ክፍያ በመክፈል ከቦታ ወደ ቦታ የመጓጓዝ መብት አላቸው፡፡

10. በጉዞ ወቅት ለጠፉ፣ ለተበላሹና ጉዳት ለደረሰባቸው እቃዎቻቸው በህግ መሠረት ከትራንስፖርት ክፍያው ጭምር የማካካሻ ክፍያ ከኦፕሬተሩ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

11. ለንግድ ካልሆነ በስተቀር ለዕለት የሚጠቀሙበትን (ልብስ፣ ምግብ፣ ወዘተ...) እስከ 25 ኪ.ግራም ክብደት ያለው ዕቃ በነፃ የማጓጓዝ መብት አላቸው፡፡

12. ከ25 ኪሎግራም በላይ ላለው ክብደት ብቻ በወቅቱ የትራንስፖርት ባለስልጣን በሚያወጣው ታሪፍ መሰረት ኪሎግራም/ኪሎ ሜትር የተሰላ ትክክለኛ ክፍያ ብቻ የመክፈል መብት አለው፡፡

13. መናኸሪያ ይዘውት የሚገቡትን ከ25 ኪሎ ግራም የማይበልጥ ዕቃ ያለ ምንም ክፍያ በመናኸሪያ ጫኝና አውራጆች የማስጫንና የማስወረድ መብት አላቸው፡፡

14. የትራንስፖርት ክፍያው የተሣፋሪውን 25 ኪሎግራም ጭነት የማስጫኛና የማውረጃ ገንዘቡን ጨምሮ የተሠራ ስለሆነ ተሣፋሪውን ገንዘብ መጠየቅ የለበትም፡፡

15. በጉዞ ወቅት የክፍያ ደረሰኝ የጠፋባቸው ወይም የተቀደደባቸው ተሣፋሪዎች ከቀሪ ደረሰኝ ላይ ስማቸው ታይቶ ተሣፋሪዎች እነርሱን የሚገልፅ መታወቂያ፣ መንጃ ፈቃድ ወይም ሌላ ማረጋገጫ ካቀረቡ ያለተጨማሪ ክፍያ የመጓዝ መብት አላቸው፡፡

16. ተሣፋሪዎች በሾፌሩ፣ በትኬት ቆራጩ፣ በረዳቱ፣ በሌላ ተሳፋሪ፣ በተራ አስከባሪ ወይም በሌላ ማንኛውም ሰው እንግልት፣ ስድብ፣ ድብደባ ወይም ሌላ ክብርን የሚነካ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ማድረግ ህገመንግስታዊ መብታቸው በመሆኑ ሰብአዊ መብታቸው ተጠብቆ የሕዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት የማግኘት መብት አላቸው።

17. ተሣፋሪዎች የመነሻና መድረሻ፣ መመገቢያ፣ ማረፊያ፣ ቦታና ሰዓት፣ የኦፕሬተሩን ማንነትና ሌሎችንም ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃዎችን ከሾፌሩ ጀርባ በሚገኝ ሰሌዳ ላይ የማግኘት መብት አላቸው።

18. እንደአመቺነቱ አስፈላጊ በሆነ የአውቶብሱ አካል ላይ መረጃዎችን መለጠፍና በትኬት ቆራጩና ረዳቱ አስረጅነት አስፈላጊ መረጃዎችን የማግኘት መብት አላቸው።

19. ተሣፋሪዎች ጉዞው ከመጀመሩ ከአንድ ሰዓት ቀደም ብለው ጉዞውን መሰረዛቸውን ለኦፕሬተሩ/ለድርጅቱ ካሳወቁ የከፈሉት ገንዘብ በሙሉ ይመለስላቸዋል።

20. ሆኖም ተሣፋሪው ዘግይቶ ከደረሰ እና መኪና ጥሎት ከሄደ 10 በመቶ ተቀናሽ ሆኖ ይመለስለታል።

21. ነገር ግን ተሳፋሪው የዘገየው ወይም ጉዞ መሰረዙን ያላሳወቀው ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት(ለምሳሌ፣ ህመም ፣ መርዶ፣አደጋ አጋጥሞት፣ወይም በፖሊስ ቁጥጥር ስር ሆኖ፣ እና በመሳሰሉት) መረጃ ማቅረብ ከቻለ የከፈሉት ገንዘብ በሙሉ ይመለስላቸዋል።

22. መኪናው ሰዓቱ ከመድረሱ በፊት ቀድሞ ከወጣ ግን ለተሳፋሪው የከፈለውን ገንዘብ በሙሉ መልሶ 10 በመቶ ተጨማሪ ካሳ ከፍሎ በህዝብ ትራንስፖርት አፈፃፀም መመሪያው መሰረት ተጨማሪ ቅጣት እንዲከፍል ይደረጋል።

23. ተሳፋሪው የዘገየው ወይም ጉዞ መሰረዙን ያላሳወቀው ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት(ለምሳሌ፣ ህመም ፣ መርዶ፣አደጋ አጋጥሞት፣ወይም በፖሊስ ቁጥጥር ስር ሆኖ፣ እና በመሳሰሉት) ከሆነ በ5 ቀናት ውስጥ

መረጃ ማቅረብ አለበት፡፡ ከ6 ቀናት እስከ 10 ቀናት ዘግይተው ለሚያሳውቁ ግን ከከፈሉት ገንዘብ 10% ተቀናሽ ሆኖ ይመለስላቸዋል፡፡ ከ10 ቀናት በኋላ ጥያቄ ለሚያቀርቡ ምንም ገንዘብ አይመለስም፡፡

24. ከተሣፈሩበት መኪና የሚወጣ ለጆሮ አደገኛ የሆነና የሚረብሽ ድምፅ ሳይሰሙ ከቦታ ወደ ቦታ የመጓጓዝ መብት አላቸው፡፡

25. ተሳፋሪው በመረጠው የንግድ፣ የህዝብ ተሽከርካሪ ሞዴልና ደረጃ (1ኛ፣2ኛ ወይም 3ኛ) የመጓጓዝ መብት አለው፡፡

26. በመናህሪያ አገልግሎት (የመፀዳጃ፣ መስተንግዶ፣ የመጠለያ፣ የጉዞ አገልግሎት ወይም ሌላ) አሰጣጡን በተመለከተ ችግሮች ካሉ ለመንግስት ተቆጣጣሪ አካል ለትራንስፖርት ባለሥልጣን/ቢሮዎች .... ወዘተ በስልክ፣ በፅሑፍ ወይም በሌላ መንገድ መረጃ የመስጠት መብት አላቸው፡፡

27. መንግስት የታሪፍ ለውጥ ሲያደርግ ተሣፋሪዎች በፌዴራል ትራንስፖርት ወይም በክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች የታሪፍ ለውጥ ትክክለኛነት ጠይቆ መረጃ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

28. በጉዞ ወቅት ረስተውት የወረዱትን እቃ እንዲመለስላቸው የተሽከርካሪውን ሰሌዳ ቁጥር፣ የጐን ቁጥር፣ የከፈሉበትን ደረሰኝ ወይም ሌላ አስፈላጊ መረጃ በመስጠት እንዲመለስላቸው የመጠየቅ ሲገኝም መታወቂያቸውን ወይም መንጃ ፈቃዳቸውን ወይም ፓስፖርታቸውን ወይም ሌላ ራሳቸውን የሚገልፅ መረጃ በማቅረብ የመውሰድ መብት አላቸው፡፡

29. በጉዞ ወቅት ችግር ሲገጥማቸው በሾፌሩ አማካኝነት እና የተሳፈረ የህክምና ባለሙያ ካለ ትብብር በመጠየቅ የመጀመሪያ እርዳታ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

30. በወንበር ቁጥራቸው መሠረት የመቀመጥ መብት አላቸው፡፡

31. የሾፌሩን፣ የገንዘብ ተቀባዩንና የረዳቱን ሥምና ስልክ ቁጥር ጠይቀው መረጃ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

32. ለከፈሉት የአገልግሎት ክፍያ ትክክለኛ ደረሰኝ የማግኘት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም መታወቂያቸውን በማሳየት ፋክቱር አሰርቶ የመውሰድ መብት አላቸው፡፡

33. ያስጫኑት እቃ በጉዞ ወቅት ምንም ጉዳት ሳይደርስበት የመረከብ መብት አላቸው፡፡ ተሰባሪ እቃ ከሆነ ተሳፋሪው በትራፊክ አደጋ ግጭት መከላከያ ፎም እቃውን በትክክል አስሮ በጥንቃቄ እንዲጫንለት የማድረግ መብት አለው፡፡

34. የእቃ መለያ ታግ እቃቸው ላይ እንዲታሰርላቸው እና ቀሪውንም እንዲይዙ የማስደረግ መብት አላቸው፡፡

35. ሾፌሮች መኪና በማሽከርከር ላይ እያሉ በተንቀሳቃሽ ስልካቸው ደንበኞቻቸውን ካነጋገሩ ተሳፋሪው ሾፌሩን ስልክ እንዳያነጋግር ወይም መኪናውን ወደ ዳር ወጣ አድርጎ እንዲያቆም የማስደረግ መብት አለው፡፡

## 3. <u>የተሣፋሪ ግዴታዎች</u>

1. ተሳፋሪዎች የመጓጓዣውን ክፍያ በወቅቱ ታሪፍ መሠረት የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡

2. ትኬቶች ከመቁረጡ በፊት አብረው የሚጓዙ ልጆች መኖር አለመኖራቸውን እና እድሜያቸውን ለትኬት ቆራጩ የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

3. ተሳፋሪዎች ከተሽከርካሪው መነሻ ሰዓት 30 ደቂቃ በፊት መናኸሪያ የመገኘት ግዴታ አለባቸው፡፡ የመነሻ ሰዓቱን አሳልፎ በቦታው የተገኘ ተሣፋሪ የከፈለውን ገንዘብ የመጠየቅ መብት ያለው ቢሆንም ገንዘብ እንዲመለስለት ሲጠየቅ 10 በመቶ ተቀናሽ ሆኖ ይመለስለታል፡፡

4. በእጅ የሚንጠለጠሉ ቦርሳዎች፣ ሻንጣዎች ወይም ሌላ የእቃዎች መያዣ ወንበር ሥር ወይም ለእቃ መጫኛ የመኪናው አካል ውስጥ በተሰራ መጫኛ በቀላሉ የሚቀመጡ እቃዎችን ብቻ የመጫን ግዴታ አለባቸው፡፡

5. ክብደታቸው 25 ኪሎ ግራም የሚበልጡ እቃዎችን የሚይዙ ከሆነ ትራንስፖርት ባለችልጣን ባወጣው የወቅቱ ታሪፍ መሰረት ክፍያ ይከፍላሉ። ክብደታው ከ 25 ኪሎ ግራም የሚበልጡ እቃዎችን ከላይ እየተመጣጠነ መጫን ግዴታ አለባቸው።

6. በተሽከርካሪውና ተሳፋሪዎች ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ኬሚካሎችና አሲዲች መጫን ፈፅሞ የተከለከለ ነው።

7. የተጠቀሙበትን ሶፍት፣ ወረቀት፣ የፍራፍሬ ልጣጭ ወይም ሌላ ቆሻሻ ለቆሻሻ ማስቀመጫ ከተዘጋጀው ቦታ ማስቀመጥ አለባቸው።

8. ተሣፋሪዎች በህጋዊ የመንግስት አካል ሲጠየቁ የከፈሉትን ትክክለኛ የገንዘብ መጠንና የከፈሉበትን ደረሰኝ ማሳየት አለባቸው።

9. የግላቸው ያልሆነ የሌላ ሰው እቃ ወይም ሻንጣ መነካካት፣ መክፈት ወይም ይዞ መውረድ የተከለከለ ነው።

10. ተጠቃሚዎች የተሽከርካሪዉን አካል የሚጐዳ ድርጊት መፈፀም የለባቸውም።

11. ለመፈተሽ ሲጠየቁ እነሱንም ሆነ ያስጫኑትን እቃ የማስፈተሽ እና ለፍተሻ የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

12. በጉዞ ላይና በመኪና ውስጥ አልኮል መጠጣት፣ ሲጋራ ማጨስ፣ ጫት መቃም፣ አደንዛዥ እፅ ወይም ሌላውን ተሣፋሪ ጤንነት የሚያውክ ድርጊት መፈፀም የተከለከለ ነው።

13. በአገልግሎት ወቅት ስለሚደርስ ቅሬታ ለሚመለከተው አካል ከማሳወቅ ውጪ ኦኘሬተሮችን መሳደብ፣ መማታት ወይም ሌላ ክብራቸውን የሚነካ ድርጊት መፈፀም የተከለከለ ነው።

14. አደገኛና የተከለከለ ነገር ወይም እቃ ለምሳሌ ፈቃድ የሌለው የጦር መሣሪያ፣ የሚፈነዱና የሚመርዙ ኬሚካሎች፣ አደንዛዥ እፆችን፣ የሰውን ልጅ ጤና የሚያውኩ ሌሎች ጭነቶች ... ወዘተ ማጓጓዝ የተከለከለ ነው።

15. ተሣፋሪዎች ለመውረድ አምሳ ሜትር ርቀት ሲቀራቸው ለረዳቱ ወይም ለሾፌሩ መናገር አለባቸው፡፡

16. ባለሀብቱ ለተሣፋሪዎች ቀበቶ አዘጋጅቶ ሁሉም ተሣፋሪዎች መኪናው ከመንቀሳቀሱ በፊት የደኅንነት ቀበቶ (Safety belts) ማሰር አለባቸው፡፡ የደኅንነት ቀበቶ (Safety belts) በተሟላ ሁኔታ ባይኖረው እንኳ ባለው መጠን ተሣፋሪዎች እንዲጠቀሙ ማድረግ አለበት፡፡

17. እንስሳትን (ዶሮ፣ ውሻ፣ ድመት.... ወዘተ) በሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ውስጥ ማጓጓዝ የተከለከለ ቢሆንም አስገዳጅ ሁኔታ ተፈጥሮ ሲጓጓዙ ጤንነታቸውን በማይጎዳ ከአካባቢው በተሰራ እቃ ውስጥ ተደርገው ከላይ ከእቃ ጋር መጫን አለባቸው፡፡

## 4. <u>የአሽከርካሪዎች ግዴታዎች</u>

1. ከመኪናው መንቀሳቀሻ ሰዓት 15 ደቂቃ በፊት በሚያሽከረክረው መኪና ውስጥ መገኘት አለበት፡፡

2. መኪናው ከመንቀሳቀሱ በፊት የመኪናውን ቴክኒካዊ ብቃት ማረጋገጥ አለበት፡፡

3. ተሽከርካሪዎችን ከማንቀሳቀሳቀሳቸው በፊት የደኅንነት ቀበቶ (Safety belts) ማሰር አለባቸው፡፡ ተሣፋሪዎችንም እንዲያስሩ ማሳሰብ አለባቸው፡፡

4. በጉዞ ወቅት የማንኛውም ኀይማኖት መዝሙርና ፊልም መክፈት የለበትም፡፡

5. በጉዞ ወቅት የማንኛውም ኀይማኖት መዝሙርና ፊልም መክፈትና ድምፁም የተሳፋሪዎችን ጤና በሚጎዳ መልኩ ማድረግ የለበትም፡፡

6. በጉዞ ወቅት የማንኛውም ኀይማኖት ቀስቃሽ ፅሁፎች ተሽከርካሪው ላይ እንዳይኖሩ ወይም እንዳይሰራጩ ማድረግ አለበት፡፡

7. በጉዞ ወቅት የማንኛውም ኀይማኖት ሰባኪ እንዳይሰብክበት ማድረግ አለበት፡፡

8. የወንበሩ አንድ ሁለተኛ /ግማሽ/ በተሣፋሪዎች ከተሞላና የመነሻ ሰዓቱ ከደረሰ ጉዞ የመጀመር ግዴታ አለባቸው፡፡

9. ከመኪናው ወንበር ቁጥር ውጪ ትርፍ ሰው መጫን በፍፁም የተከለከለ ነው፡፡

10. መኪናውን ከማንቀሳቀሳቸው በፊት መውጫና ሌሎች ለጉዞ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን መሟላታቸው ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

11. አሽከርካሪዎች ለተሣፋሪዎች በቂ የቁርስና የምሳ መመገቢያ ጊዜ መስጠት አለባቸው፡፡

12. ሕጋዊ ያልሆነ የጉዞ ፈቃድ (መውጫ) በፍፁም የተከለከለ በመሆኑ መጠቀም የለባቸውም፡፡

13. ተሽከርካሪዎቻቸውን ከማንቀሳቀሳቸው በፊት ተሣፋሪዎች በሙሉ ገብተው መቀመጣቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

14. በጉዞ ወቅት ለሚጠፋ፣ ለተበላሸ ጉዳት ለደረሰበት የተሣፋሪ እቃ በወቅቱ ዋጋ የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡

15. ታግ የተደረገበት የተገልጋዮች ንብረት ከጠፋ ኦፕሬተሩ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ ለእቃ ማጓጓዝ የተከፈለውንም ገንዘብ ለተገልጋዮች የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡

16. መኪና ከማንቀሳቀሳቸው በፊት የሚወርዱ ተሣፋሪዎች መውረዳቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

17. ባለቤት የሌለውን እቃ ማጓጓዝ የተከለከለ ነው፡፡

18. አደገኛና በሕግ የተከለከለ ነገር ለምሳሌ ያልተፈቀደ የጦር መሣሪያ፣ መርዛማና የሚፈነዱ ኬሚካሎች፣ አደንዛዥ ዕፆችን... ወዘተ ማጓጓዝ የተከለከለ ነው፡፡

19. ሾፌሮች መኪና በማሽከርከር ላይ እያሉ በተንቀሳቃሽ ስልካቸው ደንበኞቻቸውን ማነጋገር የተከለከለ ነው፡፡

Federal Democratic Republic Ministry of Transport & Communications

20. ተሽከርካሪው የቴክኒክ ብልሽት ካላጋጠመው በስተቀር ተሣፋሪዎችን ከአንድ ተሽከርካሪ ወደ ሌላው ተሽከርካሪ ማዛወር የለባቸውም፡፡

21. ከመጫኛና ማውረጃ ቦታዎች ውጪ ተሣፋሪዎችን ማሳፈርና ማውረድ የተከለከለ ነው፡፡

22. ተገቢውን የጉዞ ሠነድ ሳይዙ ለምሳሌ የተጭበረበረ የሕዝብ ማመላለሻ የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም መንጃ ፈቃድ ይዘው የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ማሽከርከር የተከለከለ ነው፡፡

23. በቅጣት ሪከርድ ምክንያት የሕዝብ ትራንስፖርት ሰነድ አጭበርብሮ ሰርቶ ወይም አሰርቶ የያዘ፣ በማንኛውም ጥፋት የታገደ ወይም የተቀጣ ለፈፀመው ጥፋት የተወሰነበትን ቅጣት ሳይከፍል ወይም ተሽከርካሪ እንዳይነዳ ታግዶ እያለ መኪና ሲያሽከረክር መገኘት የተከለከለ ነው፡፡

24. በማንኛውም የሕዝብ፣ የንግድ ማመላለሻ አገልግሎት በመስጠት ላይ እያለ የደንብ ልብስ በአግባቡ ለብሶ አለመገኘት  የተከለከለ ነው፡፡

25. ማንኛውም አሽከርካሪ በሥራ ላይ እያለ አግባብ ባላቸው የክትትል፣ የድጋፍና ቁጥጥር ሠራተኞች ወይም በሌሎች ሕጋዊ አካላት ማንኛውም መረጃ ሲጠየቅ ለማሳየት ፈቃደኛ አለመሆን ወይም እንቢተኛ ሆኖ መገኘት የተከለከለ ነው፡፡

26. በጉዞ ላይ እያለ አልኮል መጠጥ መጠጣት፣ ጫት መቃምና አደንዛዥ እፆችን መጠቀም ወይም ሲጠቀም በተጨባጭ የተገኘ ይቀጣል፡፡

27. ልዩ የውድድር ስርዓት ከሌለ በስተቀር ከተሰጠው ፈቃድ ውጪ ወይም በደረጃ ተለይቶ ለአንድ ደረጃ ብቻ ፈቃድ ተሰጥቶት ለሌላ ደረጃ በተፈቀደ ታሪፍ አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

28. ተገልጋዩ ኅብረተሰብ ዓዙን (እቃውን) በአውቶብስ ውስጥ ረስቶ ሲሄድ ለሚሠራበት ግለሰብ ወይም ድርጅት ጽ/ቤት በወቅቱ አለማስረከብ የተከለከለ ነው፡፡

29. በጉዞ ኘሮግራም መሠረት የሥምሪት እንቅስቃሴ በአግባቡ ተግባራዊ አለማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

30. በመናኸሪያ ውስጥም ሆነ በጉዞ ላይ ተሣፋሪውን ማንገላታት፣ ማንጓጠጥ ወይም የመጉተት ተግባር መፈፀም የተከለከለ ነው።

## 5. <u>የገንዘብ ተቀባይ ግዴታዎች</u>

1. ትኬቶች ከመቁረጡ በፊት አብረው የሚጓዙ ልጆች መኖር አለመኖራቸውን እና እድሜያቸውን ጠይቆ ተገቢውን ክፍያ ገልፆ ማስከፈሉን ማረጋገጥ አለበት።
2. ጉዞ ከመጀመሩና በጉዞ ላይ እያሉ አስፈላጊ የሆኑ ትኬቶች፣ ደረሰኞችንና እቃ ማስጫኛ ታጉች በበቂ ሁኔታ መያዝና በአግባቡ መጠቀም እና አገልግሎት መስጠት አለበት።
3. ለተሣፋሪው ይሁን በተቆጣጣሪ አካላት መረጃ ሲጠየቅ ተገቢውን መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ሆኖ መገኘት አለበት።
4. ከመነሻ እስከ መድረሻ ያለው ርቀት ቢያንስ ከ50 ኪሎ ሜትር በላይ በሆነ የጉዞ ትኬት በወንበር ቁጥር በቅደም ተከተል መቁረጥ፣ በወንበር ልክ ተሣፋሪዎች እንዲቀመጡ ማድረግ፣ እንዲሁም በጉዞ ትኬቶች ላይ የተሣፋሪውን ወይም የተጓዡን ሥም መፃፍ አለበት።
5. ከሌሎች የሥራ ባልደረቦች ጋር በመሆን ለተሣፋሪዎች ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ አለበት።
6. መናኸሪያ ውስጥም ይሁን ውጪ ተሣፋሪውን መጉተት፣ ማንገላታት፣ መዝለፍና ማንጓጠጥ የለበትም።
7. ተሽከርካሪው ሳይቆም ተሣፋሪውን ለአደጋ በሚያጋልጥ ሁኔታ በር መክፈትና እንዲወርዱ ማድረግ የለበትም።
8. የሚሠራበትን የተሽከርካሪ ባለንብረት ማኅበር ወይም ድርጅትና ግለሰብ ሕጋዊ መታወቂያ፣ የደንብ ልብስና ባጅ በአግባቡ መጠቀምና መያዝ አለበት።
9. ተሣፋሪው ለከፈለው የትራንስፖርት ዋጋ ደረሰኝ መስጠት አለበት።
10. ዕቃ ላይ ታግ ማሰር አለበት።

11. የጉዞ አቅጣጫ ለተሣፋሪው መናገርና በጉዞ ወቅት የማረፊያ፣ የመመገቢያና የማደሪያ ቦታዎችን አስቀድሞ ወይም ከጉዞ በፊት መግለፅ አለበት፡፡

12. በተጭበረበረ መታወቂያ፣ ባጅና ከሥራው ጋር አግባብ በሌላቸው ሠነዶች መጠቀም ወይም ለማጭበርበር መሞከር የለበትም፡፡

13. በቅጣት ሪከርድ ምክንያት ታግዶ እያለ አገልገሎት ሲሰጥ መገኘት የለበትም፡፡

14. ተቀጣጣይነት ያላቸው እና ለተሣፋሪዎች ምቹነት የሚነሱ እንደ በርበሬ፣ እንስሳት… ወዘተ በተሽከርካሪው ውስጥ እንዲጫኑና እንዲጓጓዙ መፍቀድ የለበትም፡፡

15. የመናኸሪያ አገልግሎት መክፈል አለበት፡፡

16. ከተወሰነው ታሪፍ በላይ ማስከፈል የለበትም፡፡

17. በቴክኒክ ብልሽት ምክንያት ጉዞው ሲቋረጥ ለተሣፋሪዎች የተጓዙበትን ርቀት ወዲያውኑ አስልቶ በመቀነስ ቀሪውን ገንዘብ መመለስ አለበት፡፡

18. የቴክኒክ ብልሽት ምክንያት ጉዞው ቢቋረጥ ለትራንስፖርት ምቹና አማራጭ የሌለው ከሆነ ኦኘሬተሩ ተለዋጭ መኪና የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

19. ለተሣፋሪዎች የሚሰጣቸውን የጉዞ ደረሰኝ ሙሉ ሥም፣ የመኪናውን የጐን ቁጥር፣ የከፈሉትን የገንዘብ መጠን፣ ማኅተምና ሌሎችንም አስፈላጊ መረጃዎች ሞልቶ መስጠት አለበት፡፡

## 6. <u>የተሽከርካሪ ረዳት ግዴታዎች</u>

1. በሥራ ላይ እያለ የተወሰነውን የተሟላ የደንብ ልብስ ለብሶ መገኘት፡፡

2. ተቀጥሮ የሚሠራበትን የተሽከርካሪ ባለንብረት ማኅበር ወይም ድርጅትና ግለሰብ ሕጋዊ መታወቂያና ባጅ በአግባቡ መጠቀምና በሥራ ላይ መዋል አለበት፡፡

3. የተጭበረበረ መታወቂያ፣ ባጅና ከሥራ ጋር አግባብ በሌላቸው ሠነዶች መጠቀም ወይም ለማጭበርበር ሲሞክር አለመገኘት የለበትም፡፡

4. ባለበት የቅጣት ሪከርድ ምክንያት ታግዶ እያለ አገልግሎት መስጠት የለበትም፡፡

5. በተሣፋሪም ይሁን በተቆጣጣሪ ወይም ሌሎች አግባብነት ባላቸው አካላት መረጃ ሲጠየቅ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን አለበት፡፡

6. ከሌሎች የሥራ ባልደረቦች ጋር በመሆን ለተሣፋሪዎች ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ አለበት፡፡

7. መናኸሪያው ውስጥም ይሁን ውጪ ተሣፋሪውን የመጐተት፣ ማንገላታት፣ የመዝለፍና ማንጓጠጥ ተግባር መፈፀም የተከለከለ ነው፡፡

8. ተሽከርካሪው ሳይቆም ተሣፋሪውን ለአደጋ በሚያጋልጥ ሁኔታ በር መክፈትና እንዲወርድ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

9. የተሽከርካሪውን ንፅሕና መጠበቅ አለበት፡፡

10. የተሽከርካሪውን የቴክኒክ ብቃትና ለጉዞ ዝግጅት እየተከታተለ ማረጋገጥና ችግር ካለም ማሳወቅ አለበት፡፡

11. ሕፃናትን የያዙ ወላጆችን ወይም ሞግዚቶችን በሾፌሩ ጀርባ እና በመጨረሻው ወንበር ማስቀመጥ የለበትም፡፡ ስለዚህ ከሹፌሩ ጀርባ እና ጎን ከሚገኙ ወንበሮች ቀጥሎ 6 ህፃናት ሊያስቀምጥ የሚችሉ ወንበሮችን በክፍት አቆይቶ በህፃናት ካልተያዙ ለማንኛውም የተሳፋሪ ትኬት ቆርጦ በእኩል መብት የሚስተናገዱባቸው እንዲሆኑ መደረግ አለበት፡፡

## ክፍል 3. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

1. **መመሪያውን የማሻሻል ወይም የመሻር ሥልጣን**

   የትራንስፖርት ባለስልጣን ይህን መመሪያ ለማሻሻል ወይም ለመሻር ሥልጣን አለው፡፡

2. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

   ይህ መመሪያ የባለስልጣኑ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ተፈርሞበት ከተላለፈበት ቀንና ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

__________ቀን/2003 ዓ.ም.

*ፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን*

*አዲስ አበባ*